ምርጫና ፓርላማ

ከዓሣዬ

03/11/10

ጥንት በነበረው ዘመነ ፊውዳሉ
ኣድርባይ ከሃዲው ልክ እንደ ኣሁኑ
ከንጉሥ ፓርላማ ተመራርጠው ገብተው
ሲያንኮራፉ ነበር ከወንበር ተንጋለው ።
የሕዝብን ኣደራ ከዓዕምሮኣቸው ፍቀው
ድንገት ሲባንኑ ከእንቅልፋቸው ነቅተው፤
ጨቋኝ ዘረኛውን በሕዝብ ላይ ሹመው
ሃገርን በመክዳት ለሆዳቸው ኣድረው
ዜጋን ኣሣረዱት እጅና ጓንት ሆነው ።
ኣነሣሰ መልካም የወርሃ የካቲት
ተኮላሽቶ ባይቀር በታጠቀው ፋሺስት
ጭራሽ ይባሥ ብሎ ዘረኛው ሲገድለው
ደግሞ እንዳይነሣ ፣ ግንቦቴው/ጲላጦስ ፣ በኣዋጅ ቀበረው ።
ምርጫ በሚል ሽፋን የውሸት ኮርቻ
ፍርፋሪ ለቃሚው ተመርጦ ለብቻ፤
ለጎጠኛው ድልዳል ምቾቱ ታሥቦ
ሆድ ኣምላኪው ሁሉ በኣንድ ተሰባሥቦ፤
ዛሬም ግዳይ ልትጥል ፣ ግንቦት ጉድዋን ኣዝላ
ሂሣብ ላታዋርድ ፣ ይቅርታን ላትጠይቅ ፣ በዕብሪት ተወጥራ
ሽር ጉድ ትላለች ፣ ታጋዩን ረሽና ደሙን ልትዘራ ።
ዳር ድንበር በማፍረሥ ከቄየው አፍልሶ
ለም መሬቱን ሽጦ ረሃብን ኣንግሦ፤
በሃገር ንብረት ዝርፊያ ኩባንያው ከብሮ
ከድህነት ትብያ ሕዝቡ ተወርውሮ፣
ግን ከቢሊየነሮች ቁንጮው ተመዝግቦ
ጌታዬ የሚሉትን ባሮቹን ሰብሥቦ፣
ዜጋን በማሣደድ ከየቤቱ ኣፍኖ
መዳረሻቸውን በማጥፋት ሰውሮ
ይኸው ሊነግሥብን ያቅራራል ዘንድሮ ።
በዚህ ትንግርተኛ የወርሃ ግንቦት
በኣጋዚ ቅልብ ብዙሃን ረግፈውበት፣
ታጋይ ሰማዕታትን መሪዎቹ ከድተው
ብዙ ሺ እሥረኞችን ከመቶ ኣሣንሰው ፣
ይሉኝታ ቢሦቹ ዕርማቸውን በልተው
በሥቃዩ ሊሾሙ፤ቁሥላቸውን ወግተው፤
ለዘረኛው ሥራዓት ጽዋን ከፍ ኣድርገው
በፓርላማው ምርጫ የግፍ ቀንበር ጭነው
ብርሃን ታዬ ይሉናል ጨለማን ኣውርሰው
በሥነ ምግባር ደንብ ጭቆናን ኣንግሰው! ።
ኣገርን ለማዳን ቀድመህ የምትደርሰው
ቃል ኪዳን ማክበሩን ከኣባ በወረሥከው
ሁሌም ለመሠዋት ግንባር የማታጥፈው
ኧረ ኣንበሣው ተነሥ ! ገድልህን ኣሣዬው! ።